የአካዳሚክ ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ
ባሕር ዳር- ኢትዮጵያ

Office of the Academic Vice President
Bahir Dar University
Bahir Dar - Ethiopia

✉ 79 ☎ 251 – (0583) 206097 ፋክስ Fax: 251 –(0582) 20 20 25 Website: www.bdu.edu.et

ቁጥር:- 1/7632/1-12-1

ቀን:- የካቲት 21 2016

ለባሕር ዳር ቴክኖሎጅ ኢንስቲትዩት

ለኢትዮጵያ ቴክስታይልና ፋ/ቴ/ኢንስቲትዩት

ለሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ

ለቢዝነስና ኢኮኖሚክ ኮሌጅ

ለሳይንስ ኮሌጅ

ለትምህርት ኮሌጅ

ለግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ

ለሶሻል ሳይንስ ፋኩልቲ

ለሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

ለመሬት አስተዳደር ኢንስቲትዩት

ለሕግ ት/ቤት

ለሥነ-ምድር ሳይንስ ት/ቤት

ለአደጋ መከላከልና ም/ዋ/ፕ/ኢንስቲትዩት

ለባዮቴክኖሎጅ ኢንስቲትዩ

ለስፖርት አካዳሚ

<u>ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣</u>

ጉዳዩ:- <u>መመሪያ ስለመላክ</u>

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሴኔት ጉባዔ ጥቅምት 15 ቀን 2016 ዓ.ም ያፀደቀውን የአገር ውስጥ መምህራን ምልመላ፣ ቅጥር፣ ዝውውርና ልማት ስርዓት ለመደንገግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 01/2016 13 ገጽ ከዚህ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እየገለፅን በዚሁ መሰረት ተፈፃሚ እንዲሆን እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር!

እሰይ ከበደ ሙሉነህ (ዶ/ር)
አካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት

Federal Democratic Republic of Ethiopia Bahir Dar University

ግልባጭ//

- ለፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
- ለአካዳሚክ ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
- ለአስተዳደር ጉ/ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
- ለምርምርና ማ/አ/ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
- ለአካዳሚክ ጉዳዮች ኤክስኪዩቲቭ ዳ/ጽ/ቤት
- ለድህረ ምረቃ ት/ቤት
- ለመምህራን ጉዳዮች ዳይሬክተር
- ለሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለሰው ኃብት አስተዳደር እና ልማት ዳይሬክቶሬት

<u>ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣</u>

# በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአገር ውስጥ መምህራን ምልመላ፣ ቅጥር፣ ዝውውርና ልማት ስርዓት ለመደንገግ የወጣ መመሪያ

**መመሪያ ቁጥር 01/2016**

ጥቅምት 15/2016 ዓ/ም

ማውጫ

ገጽ

መግቢያ ........ 1
ክፍል አንድ፡ አጠቃላይ ጉዳዮች ........ 1
1.1. አጭር ርዕስ ........ 1
1.2. የመመሪያው ዓላማ ........ 2
1.3. የተፈፃሚነት ወሰን ........ 2
1.4. የፆታ አገላለጽ ........ 2
ክፍል ሁለት፡ የመምህራን አመላመል መርሆች ........ 2
ክፍል ሶስት፡ የመምህራን ቅጥርና ዝውውር ሥርዓት ........ 3
3.1. የቅጥር አፈፃፀም ዘዴዎች ........ 3
3.2. አጠቃላይ መርሆዎች ........ 3
3.3. መለያ መስፈርቶችና ዋጋቸው ........ 4
3.4. አካዳሚክ እርከኖችና ሥራ ላይ የሚውሉ መስፈርቶች ........ 7
3.5. የመምህራን ቅጥር አፈፃፀም ........ 10
ክፍል አራት፡ የመምህራን ልማትን በተመለከተ ........ 11
4.1. የረዳት ምሩቃን በተመለከተ የሚከናወኑ የመምህራን ልማት ሥራዎች ........ 11
4.2. በሌክቸረርነት የሚቀጠሩ መምህራንን በተመለከተ የሚከናወኑ የመምህራን ልማት ሥራዎች ........ 12
4.3. የአገር ውስጥና የውጭ አገር ስኮላርሽፕ ምልመላና መረጣ መስፈርቶች፡ ........ 12
4.4. ቀጣይ ትምህርት እድሎችና ሥልጠና አፈፃፀም፡ ........ 12
ክፍላ አምስት፡ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ........ 13
5.1. እኩል የመቀጠር መብትን በተመለከተ ........ 13
5.2. የተሻሩና የተተኩ አሰራር ሥርዓቶችን በተመለከተ ........ 13
5.3. መመሪያውን ስለማሻሻል ........ 13
5.4. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ ........ 13

## መግቢያ

የኢፌዴሪ መንግስት ትምህርትና ስልጠና ፍኖተ ካርታ መሰረት ዩኒቨርሲቲዎች በተልዕኮና በትኩረት መስክ ሲደራጁ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ሆኖ እንዲደራጅ በትምህርት ሚኒስቴር የተወሰነ በመሆኑ፣

የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለመሆን ከሚያበቁ ነገሮች መካከል ከፍተኛ ብቃት (ልዩ ችሎታ) ያላቸው መምህራንና ተመራማሪዎች እንዲሁም ተማሪዎች መኖር፣ የራስን ገቢ የማመንጨትና የመጠቀም አቅም፣ እንዲሁም ለመማር ማስተማርና ምርምር የሚያገለግሉ የተደራጁ መሰረተ ልማቶች መኖርና የምርምር ውጤቶች ማውጣት በመሆኑ፣

በቅድመ ምረቃም ይሁን በድህረ ምረቃ ደረጃ ከፍተኛ አቅም ያላቸውን ተማሪዎች ለመሳብ እንዲቻል በመማር ማስተማር፣ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማ የሆኑና እንዲሁም የፕሮጀክት ንድፈ ሃሳብ በብቃት መፃፍና ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ማስገኘት የሚችሉ መምህራንና ተመራማሪዎችን በቅጥርና በዝውውር ወደ ዩኒቨርሲቲው ማምጣትና ያሉትን መምህራንና ተመራማሪዎችንም አቅም ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአገር ውስጥ መምህራን ምልመላና ቅጥርን ለመወሰን በትምህርት ሚኒስቴር የወጣው መመሪያ ቁጥር 01/2011 የመምህራንና ተመራማሪዎችን ዝውውር አፈፃፀም ያላካተተ በመሆኑ፣

ከፍተኛ የትምህርት ዝግጅት (ፒ.ኤች.ዲ ዲግሪ) ያላቸውን መምህራን ስለመቅጠር ያለውን ዝርዝር አፈፃፀም በግልፅ ያላስቀመጠና ለዩኒቨርሲቲዎች መብት የሰጠ በመሆኑ፣

የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሴኔት በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 49(3) በተሰጠው ስልጣን እና በመመሪያ ቁጥር 01/2011 አንቀጽ 6 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ፡ አጠቃላይ ጉዳዮች

### 1.1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአገር ውስጥ መምህራን ምልመላ፣ ቅጥር፣ ዝውውርና ልማት ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁጥር 01/2016 ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡

## መግቢያ

የኢፌዴሪ መንግስት ትምህርትና ስልጠና ፍኖተ ካርታ መሰረት ዩኒቨርሲቲዎች በተልዕኮና በትኩረት መስክ ሲደራጁ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ሆኖ እንዲደራጅ በትምህርት ሚኒስቴር የተወሰነ በመሆኑ፣

የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለመሆን ከሚያበቁ ነገሮች መካከል ከፍተኛ ብቃት (ልዩ ችሎታ) ያላቸው መምህራንና ተመራማሪዎች እንዲሁም ተማሪዎች መኖር፣ የራስን ገቢ የማመንጨትና የመጠቀም አቅም፣ እንዲሁም ለመማር ማስተማርና ምርምር የሚያገለግሉ የተደራጁ መሰረተ ልማቶች መኖርና የምርምር ውጤቶች ማውጣት በመሆኑ፣

በቅድመ ምረቃም ይሁን በድህረ ምረቃ ደረጃ ከፍተኛ አቅም ያላቸውን ተማሪዎች ለመሳብ እንዲቻል በመማር ማስተማር፣ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማ የሆኑና እንዲሁም የፕሮጀክት ንድፈ ሃሳብ በብቃት መፃፍና ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ማስገኘት የሚችሉ መምህራንና ተመራማሪዎችን በቅጥርና በዝውውር ወደ ዩኒቨርሲቲው ማምጣትና ያሉትን መምህራንና ተመራማሪዎችንም አቅም ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአገር ውስጥ መምህራን ምልመላና ቅጥርን ለመወሰን በትምህርት ሚኒስቴር የወጣው መመሪያ ቁጥር 01/2011 የመምህራንና ተመራማሪዎችን ዝውውር አፈፃፀም ያላካተተ በመሆኑ፣

ከፍተኛ የትምህርት ዝግጅት (ፒ.ኤች.ዲ ዲግሪ) ያላቸውን መምህራን ስለመቅጠር ያለውን ዝርዝር አፈፃፀም በግልፅ ያላስቀመጠና ለዩኒቨርሲቲዎች መብት የሰጠ በመሆኑ፣

የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሴኔት በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 49(3) በተሰጠው ስልጣን እና በመመሪያ ቁጥር 01/2011 አንቀጽ 6 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ፡ አጠቃላይ ጉዳዮች

## 1.1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአገር ውስጥ መምህራን ምልመላ፣ ቅጥር፣ ዝውውርና ልማት ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁጥር 01/2016 ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡

### 1.2. የመመሪያው ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ ዩኒቨርሲቲው የመምህራንን ቅጥር፣ ዝውውርና ልማት በብቃት ላይ የተመሰረተ፣ ግልጽና ፍትሀዊ እንዲሆን ማድረግ ነው።

### 1.3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ስር ባሉ አካዳሚክ ክፍሎች በአገር ውስጥ ኢትዮጵያዊ መምህራንና ተመራማሪዎችን ለመመልመል፣ ለመቅጠርና ለማልማት ያገለግላል።

### 1.4. የፆታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፀው በሙሉ ሴትንም ያካትታል።

## ክፍል ሁለት፡ የመምህራን አመላመል መርሆች

2.1. በዩኒቨርሲቲው ሥር ያሉ አካዳሚክ ክፍሎች አካዳሚካዊ ብቃትን፣ ለማስተማርና ለምርምር ያላቸውን ፍላጎትና ዝንባሌ እንደዚሁም ተማሪዎች የተስተካከለ ስብዕና እንዲኖራቸው ዓርአያ መሆን የሚችሉትን ከራሳቸውና ከሌሎች ከትምህርት፣ ከኢንዱስትሪውና ከምርምር ተቋማት ይመለምላሉ።

2.2. አካዳሚክ ክፍሎች ከራሳቸውና ከሌሎች ተቋማት የሚመለምሉና የሚቀጥሯቸው መምህራን ብዛት አካዳሚያዊ ባህል ብዝሃነት ማሳደግ በሚያስችል አግባብ መፈፀም ይኖርባቸዋል።

2.3. ከኢንዱስትሪ እና/ወይም ከምርምር ተቋማት መምህራንና ተመራማሪዎችን በዝውውር መቅጠር ሲፈለግ መምህራንን ለመቅጠር በዚህ መመሪያ የተቀመጠውን አነስተኛውን የመምረጫ መስፈርት የሚያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ እንደተጠበቀ ሆኖ ሲመለመሉ በተቋማቸው በሰሩባቸው ዓመታት የነበራቸውን የስራ አፈፃፀም ውጤት መሠረት ማድረግ ይኖርበታል።

2.4. አካዳሚክ ክፍሎች ከቅድመ ምረቃ ተማሪዎቻቸው ተኪ መምህራንን (ረዳት ምሩቃንን) መመልመል ቢያስፈልጋቸው የሚመለምሏቸው እጩ መምህራን የላቀ አካዳሚያዊ አፈፃፀም፣ እንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታና መልካም ስነምግባር ያላቸው መሆናቸውንና ከዚህም ባለፈ ኃላፊነት ለመውሰድ፣ ሌሎችን ለማስተባበርና ለመምራት የነበራቸው ተሳትፎና እንቅስቃሴ ከግንዛቤ ማስገባት ይኖርባቸዋል። ይህም ሲፈፀም በትምህርት ክፍሉ ካውንስል ዝርዝር ግምገማ ተደርጎ እነዚህ ተመልማዮች በአሳማኝ መስፈርት መለየታቸውን ማረጋጋጥ ያስፈልጋል።

2.5. አካዳሚክ ክፍሎች ከድህረ ምረቃ ተማሪዎቻቸው እጩ መምህራን ሲመለምሉ ይችላሉ። በዚህ ሁኔታ ምልመላ በሚካሄድ ጊዜ የላቀ አካዳሚያዊ አፈፃፀም፣ እንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታና መልካም ስነምግባር ያላቸው መሆናቸውንና በጥናትና ምርምር ያሳዩት አፈፃፀም፣ የመመረቂያ ጥናትና ምርምር ስራቸው ተገቢነትና ችግር ፈችነት በልዩ ጥንቃቄ መታየት ይኖርበታል። በሁሉም ደረጃዎች የመምህራን ቅጥርና ዝውውር አፈፃፀም ለሴት አመልካቾች ልዩ ትኩረት ይሰጣል።

## ክፍል ሶስት፡ የመምህራን ቅጥርና ዝውውር ሥርዓት

### 3.1. የቅጥር አፈፃፀም ዘዴዎች

3.1.1. ቅጥር በሁለት መንገድ ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል።

3.1.1.1. በግልፅ ማስታወቂያ አውጥቶ በማወዳደር፣

3.1.1.2. ከተመሳሳይ ወይም አቻ ተቋማት በዝውውር (ዩኒቨርሲቲው/አካዳሚክ ክፍሎች ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን መምህራንና ተመራማሪዎች በልዩ ሁኔታ በማንኛውም ጊዜ ዝውውር ሊፈጽሙ ይችላሉ)።

### 3.2. አጠቃላይ መርሆዎች

3.2.1. ሁሉም አካዳሚክ ክፍሎች የመምህራን ቅጥርን በተመለከተ ከቅደመና ድህረ ምረቃ ተማሪዎቻቸው መልምለው ከሚያስቀሯቸው/ ከሚቀጥሯቸው በስተቀር አገራዊ ተደራሽነትና ሽፋን ባለው (ጋዜጣ ወይም ቴሌቭዥን) በግልጽ ማስታወቂያ የሚፈፀም ይሆናል። በተጨማሪም የስራ ማስታወቂያው በዩኒቨርሲቲው ድረገጽ ወይም አካዳሚክ ክፍሎች ድረገጽ እና ማህበሪያዊ ሚዲያዎችና ሌሎችም መረጃ ማሰራጫ መንገዶች ተደራሽ ማድረግ ያስፈልጋል።

3.2.2. ማስታወቂያው የሚወጣበት ወቅትና ለአመልካቾች የሚሰጠው የማመልከቻ ጊዜ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን የማስመረቂያ ጊዜ፣ የማመልከቻ ቦታና የማመልከቻ ማቅረቢያ ዘዴዎች ታሳቢ ማድረግ ተመራጭ ይሆናል።

3.2.3. በአንድ የቅጥር ማስታወቂያ የሚፈለገው የተወዳዳሪ አመልካቾች ቁጥር ከ10 ካነሰ ድጋሚ ማስታወቂያ ይወጣል። ይህም ሲፈፀም በመጀመሪያው ማስታወቂያ ያመለከቱ አመልካቾች ማስታወቂያ በድጋሜ ሲወጣ ከዚህ በፊት ያመለከቱት ማመልከቻ ይያዝላቸዋል። ይህ እንዳለ ሆኖ ቢያንስ ሁለት ጊዜ ድጋሚ ማስታወቂያ ወጥቶ በቂ

አመልካቾች የማይገኙ ከሆነ ከአስር በታች አመልካቾች ቢቀርቡም በቀረቡት አመልካቾች መካል በማወዳደር ቅጥር ሊፈጸም ይችላል፡፡

3.2.4. አካዳሚክ ክፍሎች ህጉን ተከትለው ለመቅጠር አስፈላጊውን ሁሉ ጥረት ካደረጉ በኂላ ካልተሳካላቸው ከተመሳሳይ ወይም አቻ ተቋማት በዝውውር ሊቀበሉ ይችላሉ፡፡

3.2.5. አካዳሚክ ክፍሎች ከተመሳሳይ ወይም አቻ ተቋማት ዝውውር ለመፈፀም በቅድሚያ ዝውውር የሚያደርጉ አካላት መምህራንን ለመቅጠር በዚህ መመሪያ የተቀመጠውን አነስተኛውን የመምረጫ መስፈርት የሚያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

3.2.6. ማንኛዉም ዝውውር በፕሬዚዳንት እና/ወይም በአካዳሚክ ም/ፕሬዚዳንት ወይም ሳይንቲፊክ ዳይሬክተር ወይም ችፍ ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተር ሲፈቀድ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

3.2.7. ዝውውር እንደ ሁኔታዉ በግልጽ ማስታወቂያ ወይም በጥቆማ ወይም በማመልከቻ ሊፈፀም ይችላል፡፡

3.2.8. ትምህርት ክፍሎች ሌላ አማራጭ ካላጡ በስተቀር የረዳት ምሩቆች ዝውውር አይኖርም፡፡ የረዳት ምሩቆች ዝውውር በትምህርት ክፍልና በአካዳሚክ ክፍል ታምኖበት በአካዳሚክ ም/ፕሬዚዳንት ሲፈቀድ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 3.3. መለያ መስፈርቶችና ዋጋቸው

### 3.3.1. እድሜ

3.3.1.1. በረዳት ምሩቅነት የመጀመሪያ ዲግሪ ምሩቃን በመቀጠሪያቸው ወቅት እድሜያቸው ከሰላሳ አምስት (35) ዓመት መብለጥ የለበትም፡፡

3.3.1.2. በሁለተኛ ዲግሪ ተመርቀው በቀጥታ ወይም ከስራ ዓለም በሌክቸረርነት ለሚቀጠሩ በመቀጠሪያቸው ወቅት እድሜያቸው ከአርባ (40) ዓመት መብለጥ የለበትም፡፡

3.3.1.3. የፒኤችዲ (PhD) ዲግሪ ያላቸው ሆነው በረዳት ፕሮፌሰር፣ በተባባሪ ፕሮፌሰር ወይም በሙሉ ፕሮፌሰርንነት ለሚቀጠሩ በመቀጠሪያቸው ወቅት እድሜያቸው ከአምሳ (50) ዓመት መብለጥ የለበትም፡፡

3.3.1.4. ከላይ ከ3.3.1.1 እስከ 3.3.1.3 የተገለጸው ቢኖርም የግለሰቡን አስፈላጊነት እና ሌላ ማግኘት አስቸጋሪ መሆኑን አካዳሚክ ክፍሎች ካመኑበትና በአካዳሚክ ም/ፕሪዚዳንቱ ከፀደቀ ትልቁ የእድሜ ጣሪያ ሊነሳ (waived) ይችላል፡፡

3.3.2. በረዳት ምሩቅነት ለመቀጠር በአካዳሚክ አፈፃፀም የተጠቃለለ ውጤት (Cumulative GPA)

3.3.2.1. ለወንዶች፡ 3.25ና ከዚያ በላይ

3.3.2.2. ለሴቶች፡ 3.00ና ከዚያ በላይ

3.3.2.3. የአካል ጉዳተኞች፡ 2.75ና ከዚያ በላይ

3.3.2.4. ለታዳጊ ክልልና አርብቶ አደር አካባቢ ተማሪዎች 2.75ና ከዚያ በላይ

3.3.2.5. ከአንድ በላይ የበጎ ልዩነት (Affirmative action) ተጠቃሚዎች 2.50ና

3.3.2.6. ለሁሉም የህክምና ዲግሪ (የሰውና የእንስሳት ህክምና) 3.00 ነጥብና ከዚያ በላይ

3.3.3. በሌክቸረርነት ለመቀጠር በአካዳሚክ አፈፃፀም የተጠቃለለ ውጤት (Cumulative GPA)

3.3.3.1. ለወንዶች፡ ሁለተኛ ዲግሪ ውጤት 3.50ና ከዚያ በላይ እንዲሁም በመጀመሪያ ዲግሪ ውጤታቸው 3.00ና ከዚያ በላይ ያላቸው፣

3.3.3.2. ለሴቶች፡ሁለተኛ ዲግሪ ውጤት 3.35ና ከዚያ በላይ እንዲሁም በመጀመሪያ ዲግሪ ውጤታቸው 2.75ና ከዚያ በላይ ያላቸው፣

3.3.3.3. ለአካል ጉዳተኞች፡ ሁለተኛ ዲግሪ ውጤት 3.15ና ከዚያ በላይ እንዲሁም በመጀመሪያ ዲግሪ ውጤታቸው 2.75ና ከዚያ በላይ ያላቸው፣

3.3.3.4. ለታዳጊ ክልልና አርብቶ አደር አካባቢ ተማሪዎች ሁለተኛ ዲግሪ ውጤት 3.15ና ከዚያ በላይ እንደዚሁም በመጀመሪያ ዲግሪ ውጤታቸው 2.50ና ከዚያ በላይ ያላቸው፣

3.3.3.5. ከአንድ በላይ የበጎ ልዩነት (Affirmative action) ተጠቃሚዎች የሁለተኛ ዲግሪያቸው 3.10ና ከዚያ በላይ እንደዚሁም በመጀመሪያ ዲግሪ ውጤታቸው 2.50ና ከዚያ በላይ የነበራቸው ሆኖ በቆይታቸው probation ገብተው የማያውቁ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

3.3.3.6. በሌክቸረርነት የሚቀጠሩ ሁሉም (በመጀመሪያ ዲግሪያቸው በሌክቸረርነት የተመረቁትን የህክምና ዶክተሮች ሳይጨምር) ቢያንስ ሁለት ዓመት ቆይታ ያለው ድህረ ምረቃ ትምህርት የተከታተሉ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተጨማሪም በመመረቂያ ጽሑፋቸው ቢያንስ $B^+$ (Very good) ወይም ተመጣጣኝ ያስመዘገቡ ሊሆኑ ይገባል፡፡

3.3.3.7. ተወዳዳሪዎች በሌላ የውጤት አያያዝ የተማሩ እንደሆነ ተመጣጣኙን በማስላት የሚያዝላቸው ይሆናል፡፡

3.3.3.8. በውጭ አገራት ትምህርታቸውን የተከታተሉ ተወዳዳሪዎች በህግ ስልጣን በተሰጣቸው አካላት የትምህርት ደረጃ አቻ ግምትና የሰነድ ማረጋገጫ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

3.3.3.9. በአካዳሚክ ውጤት እጩዎችን ለመለየት የተቀመጠው አነስተኛው መስፈርት እንደተጠበቀ ሆኖ ያመለከቱት ተወዳዳሪዎች ቁጥር በዛ ያለ ሆኖ ሲያገኙት አካዳሚክ ክፍሎች ከፍ ያለ የመቁረጫ ነጥብ ያመጡትን ብቻ ለቀጣይ ውድድር በውጤታቸው ብቻ ሊለዩዋቸው ይችላሉ፡፡ በዛ ያሉ አመልካቾች ቀርበዋል ተብሎ የሚወሰደው ለአንድ ክፍት መደብ ሃያ (20) ና ከዚያ በላይ አመልካቾች የቀረቡ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ይህ ሲፈፀምም ለእያዳንዱ ክፍት መደብ ቢያንስ አስር (10) አመልካቾች ለመጨረሻ ማጣሪያ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

3.3.4. በረዳት ፕሮፌሰር ለመቀጠር

3.3.4.1. የፒኢችዲ ዲግሪ (PhD) ወይም አቻ ወይም ሜዲካል ዶክተር (MD) እና የስፔሻላይዜሽን ሰርቲፊኬት ያለው ወይም አቻ ወይም በእንስሳት ህክምና ዶክትሬት ዲግሪ (DVM) እና በሙያው ሁለተኛ ዲግሪ ያለው ወይም አቻ፡፡

3.3.4.2. በተጨማሪም በሁለተኛና ሶስተኛ ዲግሪ የመመረቂያ ጽሑፋቸው ቢያንስ $B^+$, Very good ወይም ተመጣጣኝ ያስመዘገቡ ሊሆኑ ይገባል፡፡

3.3.5. በተባባሪ ፕሮፌሰር ለመቀጠር

3.3.5.1. የፒኢችዲ ዲግሪ (PhD) ወይም አቻ ወይም ሜዲካል ዶክተር (MD) እና በሰብ ስፔሻላይዜሽን ሰርቲፊኬት ያለው ወይም አቻ ወይም በእንስሳት ህክምና ዶክትሬት ዲግሪ (DVM) እና በተጨማሪም በሶስተኛ ዲግሪ (ፒኤችዲ) የተመረቀ፣

3.3.5.2. እውቅና ካለው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የተባባሪ ፕሮፌሰርነት እድገት ያገኘና ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለተባባሪ ፕሮፌሰርነት የሚጠይቀውን ዝቅተኛ የህትመት ደረጃ የሚያሟላ፣

3.3.5.3. በተጨማሪም በሁለተኛና ሶስተኛ ዲግሪ የመመረቂያ ጽሑፋቸው ቢያንስ $B^+$, Very good ወይም ተመጣጣኝ ያስመዘገቡ ሊሆኑ ይገባል፡፡

3.3.6. በሙሉ ፕሮፌሰር ለመቅጠር

3.3.6.1. የፒኢችዲ ዲግሪ (PhD) ወይም አቻ ወይም ሜዲካል ዶክተር (MD) እና በሰብ ስፔሻላይዜሽን ሰርቲፊኬት ያለው ወይም አቻ ወይም በእንስሳት ህክምና ዶክትሬት ዲግሪ (DVM) እና በተጨማሪም በሶስተኛ ዲግሪ (ፒኤችዲ) የተመረቀ፣

3.3.6.2. እውቅና ካለው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የፕሮፌሰርነት እድገት ያገኘና ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለሙሉ ፕሮፌሰርነት የሚጠይቀውን ዝቅተኛ የህትመት ደረጃ የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡

## 3.4. አካዳሚክ እርከኖችና ሥራ ላይ የሚውሉ መስፈርቶች

3.4.1. ከመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች መካከል ተመልምለው በረዳት ምሩቅነት ለሚቀጠሩ ስራ ላይ የሚውሉ መስፈርቶች

3.4.1.1. አካዳሚካዊ አፈፃፀም የተሰጠው ክብደት 35 ከመቶ ሲሆን አራት (4) ነጥብ የመመረቂያ ውጤት ያለው ሙሉ 35 ነጥብ የሚያገኝ ሲሆን ሌላው እንደ ነጥቡ መጠን በመቶኛ እየተሰላ ይፈፀማል፡፡

3.4.1.2. የሚቀጠሩበት ትምህርት መስክ የእንግሊዘኛ ቋንቋ የጽሑፉ ፈተና ውጤት (35)

3.4.1.3. ለመምህርነት ሙያ ያለው ፍቅር፣ ፍላጎትና ዝግጅት ጨምሮ የሚታይበት ቃለ መጠይቅ (20)

3.4.1.4. ከትምህርት ክፍሉ መምህራን የሚሰጥ ምስክርነት (Recommendation) (10)፡፡ ምስክርነት ሲፃፍ Ethics, Extra curricula and Role and Cordination መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡

3.4.2. በመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቀው ከስራ ዓለም ከሌሎች ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ከኢንዱስትሪውና ከምርምር ተቋማት ለሚቀጠሩ ሥራ ላይ የሚውሉ መስፈርቶች

3.4.2.1. አካዳሚካዊ አፈፃፀም የተሰጠው ክብደት 35 ከመቶ ሲሆን አራት (4) ነጥብ የመመረቂያ ውጤት ያለው ሙሉ 35 የሚያገኝ ሲሆን ሌላው እንደ ነጥቡ መጠን በመቶኛ እየተሰላ ይፈፀማል፡፡

3.4.2.2. የሚቀጠሩበት ትምህርት መስክ የእንግሊዘኛ ቋንቋ የጽሑፍ ፈተና ውጤት (35)

3.4.2.3. ምስለ ማስተማር (Demo) (20)

3.4.2.4. ለመምህርነት ሙያ ያለው ፍቅር፣ ፍላጎትና ዝግጅት ጨምሮ የሚታይበት ቃለ መጠይቅ (10)

3.4.3. ከድህረ ምረቃ ተማሪዎች መካከል በሌክቸረርነት ለሚቀጠሩት ሥራ ላይ የሚውሉ መስፈርቶች

3.4.3.1. አካዳሚካዊ አፈፃፀም የተሰጠው ክብደት 30 ከመቶ ሲሆን አራት (4) ነጥብ የመመረቂያ ውጤት ያለው ሙሉ 30 የሚያገኝ ሲሆን ሌላው እንደ ነጥቡ መጠን በመቶኛ እየተሰላ ይፈፀማል፡፡

3.4.3.2. የጽሑፍ ፈተና ውጤት (30)

Federal Democratic Republic of Ethiopia Bahir Dar University

3.4.3.3. ለመምህርነት ሙያ ያለው ፍቅር፣ ፍላጎትና ዝግጅት ጨምሮ የሚታይበት ቃለ መጠይቅ (10)

3.4.3.4. የመመረቂያ ወረቀቱን በማቅረብ በትምህርት ክፍሉ ሙያተኞች ፓናል የሚሰጠው ውጤት (30)

3.4.4. በሁለተኛ ዲግሪ ተመርቀው ከስራ ዓለም ከሌሎች ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ከኢንዱስትሪና ከምርምር ተቋማት ለሚቀጠሩ ሥራ ላይ የሚውሉ መስፈርቶች

3.4.4.1. አካዳሚካዊ አፈፃፀም የተሰጠው ክብደት 30 ከመቶ ሲሆን አራት (4) ነጥብ የመመረቂያ ውጤት ያለው ሙሉ 30 የሚያገኝ ሲሆን ሌላው እንደ ነጥቡ መጠን በመቶኛ እየተሰላ ይፈፀማል፡፡

3.4.4.2. የጽሑፍ ፈተና ውጤት (30)

3.4.4.3. ምስለ ማስተማር (Demo) (10)

3.4.4.4. ለመምህርነት ሙያ ያለው ፍቅር፣ ፍላጎትና ዝግጅት ጨምሮ የሚታይበት ቃለ መጠይቅ (10)

3.4.4.5. የመመረቂያ ወረቀቱን በማቅረብ በትምህርት ክፍሉ ሙያተኞች ፓናል የሚሰጠው ውጤት (20)

3.4.5. በረዳት ፕሮፌሰርነት ለሚቀጠሩት ሥራ ላይ የሚውል መስፈርቶች

3.4.5.1. የሁለተኛ ዲግሪ አካዳሚካዊ አፈፃፀም የተሰጠው ክብደት 30 ከመቶ ሲሆን አራት (4) ነጥብ የመመረቂያ ውጤት ያለው ሙሉ 30 የሚያገኝ ሲሆን ሌላው እንደ ነጥቡ መጠን በመቶኛ እየተሰላ ይፈፀማል፡፡

3.4.5.2. የምርምር ህትመት የተሰጠው ክብደት 30 ሲሆን የህትመቶቹ ጥራት እና ነጥብ አያያዝ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሴኔት ሕግ ቁጥር 003/2013 አንቀጽ 101 ላይ ያለውን መሠረት ያደረገ ሆኖ ሶስት (3) እና ከዚያ በላይ የህትመት ነጥብ ያለው 30 የሚያገኝ ሲሆን ከዚህ በታች ያላቸው በመቶኛ እየተሰላ ይፈፀማል፡፡

3.4.5.3. የመመረቂያ ወረቀቱን በማቅረብ በትምህርት ክፍሉ ሙያተኞች ፓናል የሚሰጠው ውጤት (40)

3.4.6. ተባባሪ ፕሮፌሰር ከስራ ዓለም ከሌሎች ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሚቀጠሩ ሥራ ላይ የሚውሉ መስፈርቶች

3.4.6.1. የምርምር ህትመት የተሰጠው ክብደት 40 ሲሆን የህትመቶቹ ጥራት እና ነጥብ አያያዝ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሴኔት ሕግ ቁጥር 003/2013 አንቀጽ 101 ላይ ያለውን መሠረት ያደረገ ሲሆን አምስት (5) እና ከዚያ በላይ የህትመት ነጥብ ያለው 40 የሚያገኝ ሲሆን ከዚህ በታች ያላቸው በመቶኛ እየተሰላ ይፈፀማል፡፡

3.4.6.2. ፕሮጀክት የተሰጠው ክብደት 10 ሲሆን በዋና ተመራማሪነት በአንድ የውጭ ፕሮጀክት የተሳተፈ ሰባት (7) ነጥብ እና በአንድ (1) የውጭ ፕሮጀክት በረዳት ተመራማሪነት የተሳተፈ ሶስት (3) ነጥብ የሚሰላ ሲሆን የነጥቡ ጣሪያ አስር (10) ነጥብ ይሆናል፡፡

3.4.6.3. አማክረው ላስመረቋቸው ተማሪዎች ብዛት የተሰጠው ክብደት 20 በመቶ ሲሆን ከዚህ ክብደት 15 በመቶ የሚሆነው ፒ.ኤች.ዲ ተማሪዎችን ለመማከርና 5 ከመቶ ክብደት ደግሞ ሁለተኛ ዲግሪ ተማሪዎችን ለማማከር ይሆናል፡፡ በዚህም መሠረት ለፒ.ኤች.ዲ በዋና አማካሪነት ለእያንዳንዱ ተማሪ 3 (ሶስት) ነጥብ እንዲሁም ለረዳት አማካሪነት 1.5 ነጥብ፤ ለማስተርስ ተማሪዎች ደግሞ በዋና አማካሪነት ለእያንዳንዱ ተማሪ 0.5 ነጥብ፣ በረዳት አማካሪ 0.25 ነጥብ እየተባዛ የሚሰጠው ሲሆን የነጥቡ የመጨረሻ ጣሪያ በፒኤችዲ (PhD) ዲግሪ አማክሮ ላስጨረሰ 15 እንዲሁም በሁለተኛ ዲግሪ አማክሮ ላስጨረሰ 5 በድምሩ 20 ነጥብ ይሆናል፡፡ ሆኖም ለማስተርስ ተማሪዎች የማማከር አገልግሎት ያልሰጠ አመልካች ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር በላይ የፒ.ኤች.ዲ ተማሪዎችን አማክሮ ከሆነ ድምር ነጥቡ 20 እስኪሞላ ድረስ የፒ.ኤች.ዲ ተማሪዎችን ለማማከር የተሰጠው ነጥብ ሊያዝለት ይችላል፡፡

3.4.6.4. ጥናታዊ ወረቀታቸውን በማቅረብ በትምህርት ክፍሉ ሙያተኞች ፓናል የሚሰጠው ውጤት (30)

3.4.7. በሙሉ ፕሮፌሰር ከስራ ዓለም ከሌሎች ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሚቀጠሩ ሥራ ላይ የሚውሉ መስፈርቶች

3.4.7.1. የምርምር ህትመት የተሰጠው ክብደት 45 ሲሆን የህትመቶቹ ጥራት እና ነጥብ አያያዝ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሴኔት ሕግ ቁጥር 003/2013 አንቀጽ 101 ላይ ያለውን መሠረት ያደረገ ሲሆን አስር (10) እና ከዚያ በላይ የህትመት ነጥብ ያለው 45 የሚያገኝ ሲሆን ከዚህ በታች ያላቸው በመቶኛ እየተሰላ ይፈፀማል፡፡

3.4.7.2. ፕሮጀክት የተሰጠው ክብደት 10 ሲሆን በዋና ተመራማሪነት በዋና ወይም በረዳት ተመራማሪነት በውጭ ፕሮጀክት የተሳተፈ አስር (10) ነጥብ የሚያገኝ ሲሆን ነጥብ አያያዝን በተመለከተ በዋና ተመራማሪነት በውጭ ፕሮጀክት ላይ የተሳተፈ በየአንዳንዱ ፕሮጀክት አራት ነጥብ በረዳት ተመራማሪነት ሁለት ነጥብ እየታሰበ የነጥብ ጣራው አስር ሆኖ የሚያዝ ይሆናል፡፡

3.4.7.3. አማክረው ላስመረቋቸው ተማሪዎች ብዛት የተሰጠው ክብደት 30 በመቶ ሲሆን ከዚህ ክብደት 24 በመቶ የሚሆነው ፒ.ኤች.ዲ ተማሪዎችን ለመማከርና 6

ከመቶ ክብደት ደግሞ ሁለተኛ ዲግሪ ተማሪዎችን ለማማከር ይሆናል፡፡ በዚህም መሠረት ለፒ.ኤች.ዲ በዋና አማካሪነት ለእያንዳንዱ ተማሪ 3 (ሶስት) ነጥብ እንዲሁም ለረዳት አማካሪነት 1.5 ነጥብ፤ ለማስተርስ ተማሪዎች ደግሞ በዋና አማካሪነት ለእያንዳንዱ ተማሪ 0.5 ነጥብ፣ በረዳት አማካሪ 0.25 ነጥብ እየተባዛ የሚሰጠው ሲሆን የነጥቡ የመጨረሻ ጣሪያ በፒኤችዲ (PhD) ዲግሪ አማክሮ ላስጨረሰ 24 እንዲሁም በሁለተኛ ዲግሪ አማክሮ ላስጨረሰ 6 በድምሩ 30 ነጥብ ይሆናል፡፡ ሆኖም ለማስተርስ ተማሪዎች የማማከር አገልግሎት ያልሰጠ አመልካች ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር በላይ የፒ.ኤች.ዲ ተማሪዎችን አማክሮ ከሆነ ድምር ነጥቡ 30 እስኪሞላ ድረስ የፒ.ኤች.ዲ ተማሪዎችን ለማማከር የተሰጠው ነጥብ ሊያዝለት ይችላል፡፡

3.4.7.4. ጥናታዊ ወረቀታቸውን በማቅረብ በትምህርት ክፍሉ ሙያተኞች ፓናል የሚሰጠው ውጤት (15)

3.4.8. በሁሉም ዉድድሮች ለሴቶች 3% እና ለአካል ጉዳተኞች 4% (Affirmative action) ይደመርላቸዋል፡፡

3.4.9. ከላይ በተጠቀሱት ሁሉም ቅጥሮች ላይ ተወዳዳሪዎች እኩል ነጥብ ካላቸዉ ቅድሚያ ለሴቶች የሚሰጥ ሲሆን ከአንድ በላይ ሴት ወይም ሁሉም ወንድ ከሆኑ በአላቸዉ የስራ ልምድ/አገልግሎት መሰረት ይለያሉ፡፡ የስራ ልምድ አያያዝ በየአንዳንዱ ዓመት የስራ ልምድ አንድ ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

3.4.10. በረዳት ፕሮፌሰር፣ በተባባሪ ፕሮፌሰርና በሙሉ ፕሮፌሰርነት ደረጃ ለሚወጡ የቅጥር ማስታወቂያዎች ለውድድር የሚቀርቡ አመልካቾች በምዝገባ ጊዜ ከማመልከቻቸው ጋር የፕሮጀክቶቻቸውን ዝርዝር፣ በማስተርስና በፒ.ኤች.ዲ ደረጃ ያማከሯቸውን ተማሪዎች ከምርምር ስራዎቻቸው ጋር የያዘ ዝርዝር እና በታወቁ አታሚዎች የታተሙ ምርምሮቻቸውን ዝርዝር ማቅረብ ይኖርባዋል፡፡

## 3.5. የመምህራን ቅጥር አፈፃፀም

3.5.1. በዩኒቨርሲቲው የሚቀጠር መምህር በተወሰነ ጊዜ/ዓመታት ሊታደስ የሚችል ውል መያዝ አለበት፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አስር ዓመትና ከዚያ በላይ ያስተማረ ወይም የተባባሪ ፕሮፌሰር ማዕረግ የደረሰ መምህር በቋሚነት ሊቀጠር ይችላል፡፡ በሌሎች ህጎች ተደንግገው በሰራተኛው ቅጥር መካተት ያለባቸው ጉዳዮች እንደተጠበቀ ሆነው ውሉ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡፡

3.5.1.1. የስራ ዝርዝር የሚገልፅ፤

3.5.1.2. መብትና ግዴታዎችን የሚያስቀምጥ፤

3.5.1.3. በተከታታይ ግምገማና የጊዜ ገደብ ውል የሚታደስ ወይም የሚቋረጥ መሆኑን የሚገልጽ

## ክፍል አራት፡ የመምህራን ልማትን በተመለከተ

የመምህራን ቅጥር በቀጣይነት የመምህራኑን አቅም ከማሳደግና ከማልማት ጋር መተሳሰር ይኖርበታል፡፡ አዲስ ወደ ዩኒቨርሲቲው በቅጥር የሚቀላቀሉትም ይሁን በሥራ ላይ የቆዩ ወይም ለቀጣይ ትምህርት ተልከው የሚመለሱት መምህራን መሰልጠን ያለባቸውን ሥልጠና ርዕስ መለየት ይገባል፡፡

### 4.1. የረዳት ምሩቃን በተመለከተ የሚከናወኑ የመምህራን ልማት ሥራዎች

4.1.1. ረዳት ምሩቃን ወደ ሥራው ዓለምና ወደ ዩኒቨርሲቲው ሠራተኛነት ሲቀየሩ ቢያንስ በሚከተሉት ላይ ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

4.1.1.1. በትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣

4.1.1.2. በአገራዊ የከፍተኛ ትምህርት አቅጣጫዎችና የህግ ማዕቀፎች፣

4.1.1.3. በዩኒቨርሲቲው የሴኔት ሊጂስትሌሽንና ሌሎች የውስጥ አሰራር ደንቦች፣

4.1.1.4. በዩኒቨርሲቲው ሰራተኞችና መምህራን ዲሲፒሊንና ሌሎች ተገቢነት ያላቸው መመሪያዎች፣

4.1.1.5. በመምህራን ስነ-ምግባር ኮድ፣

4.1.1.6. ለሚማሩበት የሁለተኛ ዲግሪ መስክ አስፈላጊ የሆነ ግን በቅድመ ምረቃ ትምህርት ያልተካተቱ የተጨማሪ ሥልጠናዎች እንዳስፈላጊነቱ መውሰድ፣

4.1.2. አካዳሚክ ክፍሎች ከቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ጥቂቶችን መልምለው በረዳት ምሩቅ ደረጃ ሲቀጥሯቸው ዋና ስራቸው ኮርስ ማስተማር መሆን የለበትም፡፡ ረዳት ምሩቃን ዋና መምህራንን በመርዳት የትምህርት ግባትና መረጃዎችን በማዘጋጀት የፈተና ወረቀቶችን/አሳይሜንቶችን በማረምና ቱቶሪያሎችን በመስጠት ራሳቸውን ለድህረ ምረቃ እያዘጋጁ መቆየት ይኖርባቸዋል፡፡

4.1.3. ረዳት ምሩቃን ከተመረቁበት መጀመሪያ ዲግሪ ጥቅል ጉዳዮች ውስጥ ለአካዳሚክ ካሪየር የሚሆናቸውን የትኩረት መስክ በመለየት በመስኩ የካበተ ልምድ ያለቸውን በማማከር የቀጣዩ የድህረ ምረቃ ትምህርት መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ ረዳት ምሩቃን የሚሰለጥኑበት የድህረ ምረቃ መስክ የትምህርት ክፍሉን የመምህራን ሙያ ብዝሀነት፣ የዩኒቨርሲቲውን የመምህራን ልማትና የረዳት ምሩቃን የትኩረት መስክ ምርጫ ባጣጣመ መልኩ መፈፀም ይኖርበታል፡፡

Federal Democratic Republic of Ethiopia Bahir Dar University

## 4.2. በሌክቸረርነት የሚቀጠሩ መምህራንን በተመለከተ የሚከናወኑ የመምህራን ልማት ሥራዎች

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከራሱ ረዳት ምሩቃን ለሁለተኛ ዲግሪ በመላክ ያስተማራቸውንም ይሁን ከውጭ የቀጠራቸውን የመማር ማስተማሩን ስራ ከመጀመራቸው በፊት ከላይ በረዳት ምሩቃን እንዲሰጡ ከተለዩ የስልጠና ርዕሶች በተጨማሪ፤

4.2.1. የከፍተኛ ዲፕሎማ ስልጠና፣

4.2.2. የማስተማር ስነ ዘዴ ተጨማሪ ስልጠናዎች፣

4.2.3. የዩኒቨርሲቲ የምርምር ትኩረት መስኮችና ያሉ የምርምር/ ጥናት እድሎች፣

4.2.4. መረጃ ለመያዝ፣ ለማደራጀት እና ለመተንተን የሚያግዙ ሶፍትዌሮች ስልጠና፣

4.2.5. ሌሎች እንደ ሙያ መስኩ የሚጨምሩ የስልጠና ርዕሶችን ያካትታል፡፡

## 4.3. የአገር ውስጥና የውጭ አገር ስኮላርሽፕ ምልመላና መረጣ መስፈርቶች፡

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ለሚወዳደሩ የአካዳሚክ ሰራተኞች የማወዳደሪያ መስፈርቶች በከፍተኛ ትምህርት ስኮላርሽፕ ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁጥር 916/2014 እና በሴኔት ህግ ቁጥር 003/2013 አንቀጽ 123 መሠረት ይሆናል፡፡

## 4.4. ቀጣይ ትምህርት እድሎችና ሥልጠና አፈፃፀም፡

መምህራን ከአንድ ትምህርት ደረጃ ከፍ ወዳለ የትምህርት ደረጃ ለስልጠና ሲላኩ ከዩኒቨርሲቲው ጋር ውል መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡ በመምህራኑ እና በዩኒቨርሲቲው መካከል የሚታሰረው ውል ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡፡

4.4.1. የተፈቀደው የቆይታ ርዝማኔ (በአመት)፣

4.4.2. ሰልጣኙ በትምህርት ላይ ሲቆይ የሚሰጠው ድጋፍ (ድጎማ) (ካለ)፣

4.4.3. ሰልጣኙ በትምህርት ላይ በሚቆይበት ወቅት የሚከፈለው ደመወዝ መጠን፣

4.4.4. ዩኒቨርሲቲው ሰልጣኙ መምህር ትምህርቱን በስኬት አጠናቆ ሲመለስ በሚያሟላበት እርከን መልሶ እንደሚቀጥረው፣

4.4.5. ሰልጣኙ መምህር ሥልጠና ላይ የሚቆይባቸው ዓመታት እጥፍ ዩኒቨርሲቲውን ለማገልገል መስማማቱን፣

4.4.6. ሰልጣኙ በትምህርት ላይ ሲቆይ የሚወጣበትን ጠቅላላ ወጭ (ደመወዝ፣ ድጎማ ወይም ድጋፍ፤ የምርምር ስራ ድጋፍ፣ የትምህርት ወጭ ሌሎች በራሳቸው ከፍለው የሚማሩት ከሚከፍሉት የማይበልጥ) በውል የሚቀመጥ ግዴታ መግባትና ለዚህም ዋስ ማቅረብ ያለበት መሆኑ፣

4.4.7. ለትምህርት የተሰጠውን ድጋፍ (Study Leave) ለትምህርቱና ለትምህርቱ ብቻ ማዋል እንዳለበት፡፡

## ክፍላ አምስት፡ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 5.1. እኩል የመቀጠር መብትን በተመለከተ

በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ያሉ አካዳሚክ ክፍሎች ብቃት ያላቸውን መምህራን ለመቅጠር በተለያዩ መልኩና መመዘኛዎች ብቃታቸውን ከማረጋገጥ ባለፈ በስልጠና አማራጮችና ስልቶች መካከል ልዩነት/ አድልዎ ማድረግ አይችሉም፡፡

### 5.2. የተሻሩና የተተኩ አሰራር ሥርዓቶችን በተመለከተ

ከአገር ውስጥ ኢትዮጵያዊ መምህራን ቅጥርን በተመለከተ ከዚህ ቀደም በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የወጡ የቅጥር መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ተተክተዋል፡፡

### 5.3. መመሪያውን ስለማሻሻል

በትምህርት ሚኒስቴር የተቀመጡ አነስተኛ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ዩኒቨርሲቲው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው መመሪያውን የማሻሻል ስልጣን አለው፡፡

### 5.4. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በዩኒቨርሲቲው ሴኔት ከፀደቀበት ከጥቅምት 15 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡